# ፖሊሲ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ
BOARD OF EDUCATION OF MONTGOMERY COUNTY

**ተዛማጅ ደንቦች፦** ACA, ACF, ACH, ACH-RA, GCC-RA, GKA-RA, JHC, JHC-RA
**ኃላፊነት የሚመለከታቸው ጽ/ቤቶች፦** Office of District Operations; Office of Human Resources and Development

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች ጾታዊ ትንኮሳ

A. **ዓላማ**

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩል (MCPS) ንብረት ላይ ጾታዊ/ወሲባዊ ጥቃትን ለመከልከል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ጾታዊ/ወሲባዊ ጥቃትን እንዲገነዘቡ፣ እንዲያውቁ፣ እንዲከላከሉ እና የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ ለመርዳት የተነደፉ የሙያ ትምህርት እና የትምህርት መርሃ ግብሮችን እንዲያዘጋጁ ኃላፊነት ለመስጠት።

የጾታዊ ትንኮሳ ቅሬታዎችን ለመፍታት ውጤታማ የአፈጻፀም ሂደቶችን ማዕቀፍ ለማብጀት።

B. **ጉዳዩ**

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ከዚህ በታች እንደተገለፀው ማንኛውንም ዓይነት፣ በሠራተኞች፣ በተማሪዎች ወይም በሦስተኛ ወገኖች ላይ በማንኛውም ሁኔታ የሚፈፀም ጾታዊ ትንኮሳን አይታገስም። ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ፣የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ማለት፦ በ MCPS ባለቤትነት ስር ያሉ ወይም የሚካሄዱ ት/ቤቶች ወይም ፋሲሊቲዎች፣ የ MCPS አውቶቡሶች እና ሌሎች የ MCPS ተሽከርካሪዎች፣ ወይም በባለቤትነት የሚያስተዳድራቸው ቦታዎችን ጭምር ማንኛውም ሌላ ተቋም፣ እና/ወይም ቅጥር ግቢ MCPS ስፖንሰር የሚያደርግባቸው እንቅስቃሴዎች የሚካሄዱባቸው ቦታዎች፣ ሁነቶች፣ እና MCPS ቁጥጥር የሚያደርግባቸው ጾታዊ ጥቃት የተፈፀመባቸው ቦታዎችን ያጠቃልላል።

2. ሰራተኞች፣ ተማሪዎች እና ሌላ ሶስተኛ ወገን ከጾታዊ/ወሲባዊ ጥቃት ነፃ የመሆን መብት አላቸው። ቦርዱ ሁሉም ሰው ከማንኛውም አይነት ጾታዊ ትንኮሳ ነፃ የሆነበትን የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር እና ለመጠበቅ፥ እናም ይህንን ፖሊሲ የሚጥስ ባህሪን ለመከላከል፣ ለማረም እና የስነምግባር ዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ቁርጠኛ ነው። ይህንን ፖሊሲ ለማስፈጸም በቦርዱ የሚወሰዱ እርምጃዎች ከቦርድ ፖሊሲዎች፣ ከ MCPS ደንቦች እና ከስቴትና ከፌዴራል ሕጎች ጋር የሚጣጣሙ ይሆናሉ።

3. ጾታዊ/ወሲባዊ ትንኮሳ ማለት የ 1964 የሲቪል መብቶች ሕግ አንቀጽ VII፣ በ 1972 እና በ 1991 የተሻሻለውን የህግ አንቀጽ መጣስ ሲሆን አንዳንድ አይነት የሠራተኞች፣ የተማሪዎች እና የሶስተኛ ወገን የጾታዊ/የወሲባዊ ትንኮሳዎች የ 1972 የትምህርት ማሻሻያዎችን አንቀጽ IX (Title IX) የሚጥስ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ የፆታዊ ትንኮሳ ዓይነቶች የወንጀል ድርጊት ሊሆኑ ይችላሉ፣ ይህም የወንጀል ቅጣት ያስከትላል።

4. ከዚህ በታች እንደተገለጸው በአንድ ወይም በሁለቱም ሕጋዊ መስፈርቶች መሠረት በአንድ ግለሰብ ላይ ጾታዊ/ወሲባዊ ትንኮሳ-ጥቃት ሊፈጸም ይችላል።

   a) ወሲባዊ ትንኮሳ ልክ በሥራ አቀጣጠር እና በሥራ ምደባ ላይ እንደሚደረግ አድልዎ፥ በአንድ ሰው ላይ ያልተፈለገ ወሲባዊ መነካካት፣ የወሲብ ውለታ ጥያቄ፣ እና ሌሎች ወሲባዊ ባህርይ

ያላቸው የቃል ወይም አካላዊ ድርጊቶች ናቸው። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት የወሲብ ትንኮሳ የሚሆነው –

(1) አንድ ግለሰብ ሥራ ለመቀጠር በግልጽም ሆነ በተዘዋዋሪ ያደረገ(ች)ው ሁኔታ ከሆነ (ማለትም፡- quid proquo ወሲባዊ ትንኮሳ)ይባላል፣ ወይም

(2) በአንድ ግለሰብ ለእንደዚህ አይነት ድርጊት መቀበል ወይም አለመቀበል ስራ የመቀጠር ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተፅእኖ የሚፈጥር ከሆነ፣ እና/ወይም

(3) እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት በግለሰብ የሥራ ክንውን ላይ ምክንያታዊ ባልሆነ መንገድ ጣልቃ የመግባት ወይም የሚያሰጋ፣ ጥላቻ ወይም መጥፎ የሥራ አካባቢን የመፍጠር አዝማሚያ አለው።

b) በዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት ፖሊሲ እንደተደነገገው አንድ ሰው ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ሁኔታ ካጋጠመው ወይም ካጋጠማት ድርጊቱ Title IX መሠረት በጾታዊ ትንኮሳ እርምጃ የሚያስወስድ ይሆናል።

(1) የ MCPS ተቀጣሪ እርዳታ መቀበል/መስጠት፣ጥቅማጥቅም ወይም አገልግሎት መቀበል/መስጠት፣ በግለሰቡ(ቧ) ያልተፈለገ የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን እንደ ቅድመ ሁኔታ መጠየቅ፣ ወይም

(2) በአንድ ግለሰብ የሚፈፀም ተገቢነት የሌለው ባህሪ በጣም ከባድ፣የሚበክል፣ እና በተጨባጭ አስጸያፊ ከመሆኑ የተነሳ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ ውስጥ በእኩልነት እድል ማግኘትን ይከለክላል። Title IX ላይ በተገለፀው ድንጋጌ መሠረት MCPS በሚቆጣጠራቸው ቦታዎች፣ ዝግጅቶችና ሁነቶች፣ ወይም በሌሎች MCPS በሚቆጣጠራቸው ቅሬታ አቅራቢ እና ተጠያቂ መካከል ጾታዊ ትንኮሳ/ጥቃት በተከሰተበት አውድ ላይ የተፈፀሙ ክስተት፣ ወይም ሁነት ተብሎ ይገለጻል። ወይም

(3) በዩ.ኤስ. በሴቶች ላይ ስለሚፈጸም ጾታዊ ጥቃት ህግ መሰረት፡- "ጾታዊ ድብደባ/ጥቃት፣" "የፍቅር ግንኙነት ጥቃት"፣ "የቤት ውስጥ ጠብ" ወይም "ጭቅጭቅ"።

(4) ሶስተኛ ወገን ማለት፡- ከ MCPS ሰራተኛ ወይም ተማሪ በስተቀር MCPS በሚያከናውናቸው እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚሳተፍ ወይም MCPS ንብረት ላይ የሚገኝ እና MCPS ጋር ግንኙነት ያላቸው ወላጆችን/አሳዳጊዎችን ሊያካትት ይችላል፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን MCPS ንብረት ላይ የሚገኙ አስጠኚዎች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ ቬንደሮች፣ የኮንትራት ሥራ ተቋራጮች፣ አሰልጣኞች፣ እና ሌሎች ሰራተኞች እና/ወይም ተማሪዎችን ይመለከታል።

C. **አቋም**

1. የፖሊሲ ጥሰቶች የስቴት ወይም የፌዴራል ሲቪል እና/ወይም የወንጀል ሕጎችን የሚጥሱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይህ ፖሊሲ የሚመለከተው እያንዳንዱ ሰው የወንጀል ቅጣቶችን የሚያስከትል መሆኑን ስለ ድንጋጌዎቹ በማሳወቅ ረገድ የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የተቻለውን ሁሉ እንዲያደርግ/እንድታደርግ መመርያ ተሰጥቷል።

2. ይህ መመሪያ በሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ ወይም የሶስተኛ ወገን የፆታዊ ትንኮሳና ጥቃት ክስተቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። በሠራተኞች፣ በሶስተኛ ወገን ወይም በተማሪዎች የተፈጸሙ የጥቃት ክስተቶችን ሁሉ ይመለከታል።

3. በማንኛውም ሰው ላይ አንድ ጊዜ ወይም በተደጋጋሚ ወሲባዊ ትንኮሳ/ጥቃት ሊከሰት ይችላል።

4. ሰራተኛን ወይም ሶስተኛ ወገንን የሚመለከት የፆታዊ ጥቃት ሪፖርት፣ የፆታ ጥቃት የደረሰበ(ባ)ት ሰው ወይም ሶስተኛ ወገን ወይም የፆታ ትንኮሳ/ጥቃት ሊፈጸም እንደሚችል መረጃ ያለው ተመልካችን ጨምሮ በማንኛውም ሰው አማካኝነት ሪፖርት ሊደረግ ይችላል።

   a) የጾታዊ ጥቃት/ትንኮሳ ክስ/ውንጀላ ወይም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ እንደዚህ አይነት አድሎአዊ ድርጊት ሲፈጽም የተመለከተ ግለሰብ ክስተቱን ወዲያውኑ ወደ "Office of Human Resources and Development, Department of Compliance and Investigations (DCI)" ሪፖርት ማድረግ አለበ(ባ)ት። ሪፖርቱ በአካል፣ በስልክ ወይም በኢሜይል DCI@mcpsmd.org ሊደረግ ይችላል። እንደ አማራጭ፥ እንደአስፈላጊነቱ ጉዳዩን ወደ DCI እንዲመራው ሰራተኞች ርእሰ መምህራቸውን/ሱፐርቫይዘር ማነጋገር ይችላሉ።

   b) ጉዳዩ በአቤቱታ አቅራቢ(ዋ)ው ሱፐርቫይዘር አማካኝነት የተፈጸመ ጥቃት ከሆነ ወይም ከቅሬታ አቅራቢው(ዋ) ጋር በተገናኘ በስልጣን ላይ ያለ(ች) ሰው ከሆነ(ች) ሰራተኛው(ዋ) ቅሬታውን በቀጥታ ለ DCI ማቅረብ ትችላለች/ይችላል።

   c) *ሪፖርት መደረግ ያለበት* MCPS *ደንብ* ACA-RA፣ *አድሎ የሌለበት፣ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት* ላይ የተደነገገውን ሂደት በመጠቀም ነው። ስለ Title IX ጾታዊ ትንኮሳ ቅሬታ ለማቅረብ፣ ሰራተኛ(ዋ)ው MCPS ደንብ ACI-RA፣ *የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ* (MCPS) *ሰራተኞች የፆታዊ ጥቃት ምርመራ* ላይ የተገለፀውን ሂደት መከተል አለበት።

   d) ቅሬታው ወይም ሪፖርቱ እየታወቀ ሆነተብሎ ውሸት ካልሆነ በስተቀር፤ ቅሬታ ማቅረብ ወይም ወሲባዊ ትንኮሳን ሪፖርት ማድረግ የሰራተኛ(ዋ)ው ማንነት አይንፀባርቅም ወይም በሰራተኛ(ዋ)ው የወደፊት የስራ እድሎች ላይ ተጽእኖ አያመጣም።

   e) በሠራተኛ ላይ ወይም በሦስተኛ ወገን ላይ የወሲብ ጥቃት ቅሬታ በማቅረቡ(ቧ) ምክንያት የበቀል እርምጃ አይወሰድበ(ባ)ትም።

   f) በተጨማሪም ቅሬታ ባቀረበ(ች) ሠራተኛ ወይም በምርመራው ሂደት ውስጥ በሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ላይ ጣልቃ ለመግባት፣ ለመገደብ፣ ለማስገደድ፣ለማስፈራራት፣ ለማዋከብ፣ ወይም ለማድላት የሚሞክር ማንኛውም ሰው የዲስፐሊን እርምጃ ይወሰድበ(ባ)ታል።

5. በሰራተኞች እና/ወይም በሶስተኛ ወገን ሰራተኞች፣እና/ወይም ተማሪዎች የተፈፀሙ የፆታዊ ትንኮሳ ውንጀላዎች DCI ምርመራ ይደረግባቸዋል። የክልል እና የፌደራል ህጎች።

   a) የሰራተኞች እና የሦስተኛ ወገን የወሲብ ትንኮሳን ጭምር MCPS የምርመራውን ምስጢራዊነት ለመጠበቅ አስተማማኝ ጥረት ያደርጋል። የቅሬታ አቅራቢው(ዋ) ስም-ሳይገለጽ ሪፖርት ቢቀርብ እንኳ፣ MCPS ሁሉንም የወሲባዊ ትንኮሳ ሪፖርቶችን ይገመግማል፣ እና መደበኛ የቅሬታ አቀራረብ፣ ቅሬታዎችን መመርመርን እና ተገቢውን ድጋፍ የመስጠት እርምጃዎችን ጭምር አግባብነት ያለው እርምጃ ይወስዳል።

b) MCPS ህጋዊ ግዴታዎችን እና የፆታዊ ትንኮሳ ክሶችን ለመመርመር እና ጾታዊ ትንኮሳ ሲደረግ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ለመውሰድ አስፈላጊ ከሆነ ቅሬታ አቅራቢ(ዋ)ውን፣ ምስክሮቹን እና ቅሬታው የቀረበበ(ባ)ትን ግለሰብ ምስጢራዊነት ለመጠበቅ MCPS ተገቢውን ጥረት ያደርጋል።

6. የተጠረጠረው ድርጊት ጾታዊ ትንኮሳን የሚያካትት መሆኑ ከተረጋገጠ፣ MCPS መዝገቡን እና አጠቃላይ ሁኔታውን፣ የድርጊቱን አይነት እና ድግግሞሹን፣ ድርጊቱ የተከሰተበትን ሁኔታ፣ የድርጊቱን ክብደት፣ የሚያስፈራራ ወይም የሚያዋርድ ወይም አፀያፊ ድርጊት ወይም ንግግር ብቻ እንደሆነ ሪኮርዱቹን ይመለከታል። እነዚህ ምክንያቶች ከእውነታ ይልቅ በግል ሃሳብና ስሜት ላይ የተመሰረቱ እና/ወይም ተጨባጭ መሆናቸውን ይገመግሉ፣ ድርጊቱ በአቤቱታ አቅራቢ(ዋ)ው ላይ ያሳደረውን ተፅእኖ ብቻ ሳይሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ በሚገኝ ሰው ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተፅእኖ ጭምር ግምት ውስጥ በማስገባት ይገመገማል። በሚቀርበው ማስረጃ እና መስፈርት መሠረት፣ ሁኔታዎቹ በትክክል ተገምግመው ውሳኔ ይሰጥበታል።

7. ምንም እንኳን ድርጊቱ በተለይ ለማዋከብ ወይም ለማዳላት የታሰበ ባይመስልም ሰራተኞች ለስነ ምግባራቸው ተጠያቂ መሆናቸውን ማወቅ አለባቸው።

a) አፀያፊ ድርጊት፣ አፀያፊ ቀልዶችን፣ ነውረኛ ቀልዶችን፣ ወይም ተቀባይነት በሌለው ሁኔታ ስም መጥራትን፣ ማንኳሰስን፣ ማጥላላትን፣ አካላዊ ጥቃቶችን፣ ወይም ማስፈራራት፣ ማፌዝ ወይም ማሾፍ፣ ስድብ፣ ወይም ማዋረድ፣ አስጸያፊ ነገሮችን ወይም ስዕሎችን እና በሥራ ወይም በት/ቤት ሥራ አፈፃፀም ላይ ጣልቃ መግባት የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

b) ምንም እንኳን ድርጊቱ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ እንደተገለጸው የፆታዊ ትንኮሳን ትርጉም ባያሟላም ሌሎች ህጎችን፣ የቦርድ ፖሊሲዎችን እና *የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሰራተኛ ስነምግባር ደንብ* እና ሌሎች ድንጋጌዎችንና የስነምግባር ደረጃዎችን የሚጥስ ከሆነ በዚሁ መሰረት ይስተናገዳል። በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ማንኛውም ነገር ተገቢ እና ከህግ ጋር የሚጣጣም እስከሆነ ድረስ ሌሎች የቦርድ ፖሊሲዎች ወይም MCPS ደንቦች በመጣሳቸው ምክንያት የሚወሰድ የዲስፕሊን እርምጃን ለመገደብ የታሰበ አይደለም።

c) ማንኛውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ የተማሪ(ዋ)ው ዕድሜ ምንም ይሁን ምን፣ MCPS ተማሪ ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት መፈፀም፣ ወይም እንደዚህ አይነት ግንኙነትን ለማድረግ በተዘጋጀ ማንኛውም ባህሪ ውስጥ መሳተፍ የተከለከለ ነው። በዚህ ብቻ ባይገደብም የተከለከሉ ባህሪዎች *የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሠራተኛ ሥነ ምግባር ደንብ* ውስጥ የተዘረዘሩትን ሥነ ምግባር የጎደለው ምግባር ምሳሌዎችን ያካትታሉ።

8. ከጾታዊ ጥቃት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለመፍታት የ MCPS ሰራተኞች መመሪያ፣ ድጋፍ መሻት እና/ወይም ችግሩ የሚፈታበትን ስልት ማቀንቀን አለባቸው። የሰው ሃብት ልማት ጽህፈት ቤት -፣ – የሥነ ስርአት ተገዢነት፣ ምርመራ፣እና የሰራተኞች ድጋፍ ፕሮግራም (EAP) አማካኝነት ለእንደዚህ አይነት ጉዳዮች አገልግሎት ይሰጣል።

D. **ተፈላጊው ውጤት**

1. ሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች ወሲባዊ ጥቃቶችን ሪፖርት ማድረግ እንዲችሉ ይማራሉ።

2. ሪፖርት ስለማድረግ፣ ስለ ምርመራ፣ ምላሽ ስለመስጠት እና የድጋፍ እርምጃዎችን ስለመውሰድ ውጤታማ እና ሕጋዊ እርምጃዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

3. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች፣ ተማሪዎች እና ሶስተኛ ወገኖች ከወሲባዊ ጥቃት ነፃ በሆነ አካባቢ ይሠራሉ ይማራሉ።

**E. የአተገባበር ስልቶች**

1. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት፦

   a) የዚህን ፖሊሲ አፈፃፀም እና ተዛማጅ የፌዴራል እና የስቴት ህጎችን እና ደንቦችን ለማስተባበር የ Title VII እኩል የቅጥር ዕድል ኦፊሰር እና የ Title IX አስተባባሪን ይሰይማል፣

   b) የቅሬታ አፋጣኝ እና ፍትሃዊ መፍትሄ በመሻት እንደ አግባቡ የድጋፍ እርምጃዎችን የሚሰጡ የምርመራ ሂደቶችን ጭምር Title VII እና Title IX ጋር በሚጣጣም መልኩ ይህንን ፖሊሲ ለመተግበር ደንቦችን ያዘጋጃል፣

   c) ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችልና የሚደግፍ ሙያዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፤

      (1) የዚህን ፖሊሲ ተገቢ አፈፃፀም ለማረጋገጥ ለሁሉም ሠራተኞች ዓመታዊ ሥልጠና መስጠት፥ እና

      (2) ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞች እና ለሌሎች MCPS ንብረት ላይ ኃላፊነት የተሞላበት የመልካም ባህሪ የስነምግባር ደንብ/ኮድ እና ሌሎች መመሪያዎችን ይፋ ማድረግ።

2. MCPS ንብረት ላይ ለሚከሰት ተቀባይነት የሌለው ባህሪን በሚመለከት ስነምግባርን ስለማክበር ስምምነት በተደረገባቸው የስነምግባር ደንቦች እና ሌሎች ድንጋጌዎች መሠረት ማንኛውም ይህንን ደንብ የሚጥስ/የምትጥስ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሠራተኛ ላይ ተገቢ የሆነ የዲስፕሊን ቅጣት እርምጃ ይወሰዳል። የዲሲፕሊን እርምጃው በዚህ ብቻ የሚገደብ ባይሆንም የቃል ወይም የጽሑፍ ተግሳጽ፣ ሌላ የሥራ ምደባ፣ ከደረጃ ዝቅ ማድረግ፣ ከሥራ ማገድ ወይም ከሥራ የማሰናበት እርምጃን ሊያካትት ይችላል።

3. *ይህንን መመሪያ የሚጥስ ማንኛውም ተማሪ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ* (MCPS) *የተማሪ የስነምግባር ህግ* መሰረት ለጥቃቱ ተገቢ ምላሽ የሚሰጥ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበ(ባ)ታል።

4. በዚህ ብቻ የተገደበ ባይሆንም፥ አንድ ሠራተኛ በማንኛውም ጊዜ የወሲብ ጥቃትን ጭምር Title VII የመጣስ ጥርጣሬን ለአሜሪካ እኩል የሥራ ዕድል ኮሚሽን (EEOC) አቤቱታ ማቅረብ ትችላለች/ይችላል። አንድ ሠራተኛ ለ EEOC ቅሬታ ከማቅረ(ቧ)ቡ በፊት ወይም በኋላ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አቤቱታ ማቅረብ አይጠበቅበ(ባ)ትም።

   U.S. Equal Employment Opportunity Commission
   EEOC Public Portal (https://publicportal.eeoc.gov/); or
   Baltimore Field Office
   GH Fallon Federal Building
   31 Hopkins Plaza, Suite 1432
   Baltimore, MD 21201

5. በማንኛውም ጊዜ ሠራተኛ Title IX የመጣስ ጥርጣሬ ካለ ለዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት የሲቪል መብቶች ቢሮ (OCR) ቅሬታ ማቅረብ ይቻላል።

የዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት የሲቪል መብቶች ጽ/ቤት

U.S. Department of Education, Office of Civil Rights
ኤሌክትሮኒክስ የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ OCR
(http://www.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html)፣ ወይም
ዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት የሲቪል መብቶች ቢሮ

U.S. Department of Education, Office of Civil Rights
Lyndon Baines Johnson Department of Education Building
400 Maryland Avenue, SW
Washington, DC 20202-1100

6. በማንኛውም ጊዜ የሚጠረጠር የወሲባዊ/ጾታዊ ጥቃት ባህርይ ያላቸውን ወንጀሎች ሠራተኞች በቀጥታ ለሕግ አስከባሪዎች ሪፖርት ማድረግ ወይም አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ።

Montgomery County Police Department
Special Victims Investigation Division
100 Edison Park Drive
Gaithersburg, MD 20878

**F. *ግምገማ እና ሪፖርት***

1. በዚህ ፖሊሲ ድንጋጌ መሰረት ለሱፐርኢንተንደንት ሪፖርት የተደረጉ የፆታዊ ጥቃት ክስተቶች እና ሌሎች የስነምግባር ጥሰቶችን በሚመለከት በየሶስት ወሩ ለቦርዱ ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል/ታቀርባለች። የክስተቱ ሪፖርቶች ካለፈው ሩብ ዓመት ጀምሮ የተፈጸሙ ተከታታይ ክስተቶችን መረጃዎች ማካተት አለባቸው። የስነሥርአት አለማክበር ሪፖርቱ ቅሬታ፣ እና የአፈታት ሂደት ግምገማዎችን፣ እና ማሻሻያዎችን ያካትታል፥ ስልጠና የተሰጠበት ስታቲስቲክስ እና መርሃ ግብሮች፣ በሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶች፣ ቢሮዎች፣ እና የስራ ቦታዎች ላይ ያለ የስራ አካባቢ አውድ ግምገማ፤ እና ለዚህ ፖሊሲ ስኬታማ ትግበራ ጠቃሚ የሆኑ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የታቀዱ ወይም የሚከናወኑ ሌሎች ተግባራትንም ያጠቃልላል።

2. ይህ ፖሊሲ በቦርዱ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት መሰረት ቀጣይነት ባለው መልኩ ይገመገማል።

***ተዛማጅ ምንጮች፡-*** Title VII of the Civil Rights Act of 1964, as amended, 42 U.S.C. §2000e et seq; Title IX of the Education Amendments of 1972, 20 U.S.C. §1681 et seq; 29 C.F.R. §1604,11; 34 C.F.R 106.30(a); Annotated Code of Maryland, Education Article, §6-104, §6-113, §6-113.2, §7-303.1, §7-424, §7-424.1, §7-424.3, and §11-60; Annotated Code of Maryland, State Government Article, Title 20, Human Relations; Code of Maryland Regulations §13A.12.05.02; Student Code of Conduct in MCPS; MCPS Employee Code of Conduct; MCPS Guidelines for Student Gender Identity

***የፖሊሲው ታሪክ፡-*** አዲስ ፖሊሲ በውሳኔ ቁጥር 323-21 ጁን 29, 2021 ተቀባይነት አግኝቷል። በውሳኔ ቁጥር 176-23 ኤፕሪል 20 ቀን 2023 ቴክኒካዊ ማሻሻያ ተደርጎበታል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-

(1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና

(2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-

(a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣

(b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም

(c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ።  በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድጋፍ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY);  Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024